# “ ቁርጥ ቀን ”

በዓለም ዙሪያ ከጊዜ ጋር ተሽቀዳድመው ሲራመዱ፤
ሌሎች ለሰላም ለእድገታቸው አተኩረው ሲወላዱ፤

በኛዋ ሐገር ቅን፤ቁም ነገር ሳያቅዱ፤
ነግቶ መሽቶ ቀን በቀናት፣ሲዋለዱ፣
ዳዴ ሳንል ስንጓተት ሳምንታቶች ሲናጐዱ፤
በጋ ክረምት ተፈራርቀው ወር በዓመታት ሲከነዱ፣
የጊዜ አባዜ ቅጥልጥሉ የሕይዎታችን ግማዱ፤
እንደ ሰርዶ ተጠላልፏል ተጨናግፎ ዘሩ ግንዱ።

በምድራችን ዳር እስከዳር መረማመጃው መንገዱ፤
እንቅፋቱ አንኮታኩቶን የእሾህ በእሾህ ዘልማዱ፤
አንቆ ይዞን በሽምቀቁ በአንገታችን ያ ጠባቡ ተዋረዱ፤
እራስ እግሩን አጣፍሮ እይታውን አውሮ የሚሳሳብ በሆዱ።

የሕልውናችን እጣ ፈንታ የእሥሥራችን ወጥመዱ፤
አቆራኝቶ ሲፈጥዘን፣ሲገንዘን ባለጡንቻው፤ባለክንዱ፤
በእትብታችን ጉንጉን አለንጋ የሚገርፈን በጥንዱ፤
ከውስጣችን ተያይዞ አያይዞ የሚፈጀን እሳት ጭዱ።

ዘመን ትውልድ ያስቆዘመው የኋልዬሽ፤የአዙሪት አካሄዱ፤
አደናቁሮ፣ አሳውሮ መቅመቅ የሚጥለን ከጉድጓዱ፤
እድራችን ይቆም ይሆን በየተራ መዋረዱ፤መሳደዱ።

እንድንወጣ በ”ቁርጥ ቀን” በአደባባይ፤በችሎቱ ሴቱ ወንዱ፤
አንቀላፍተን በማናልፈው በማያልፈን ጉዳጉዱ፤ነጎድጓዱ፤
በየካቲት እንዲካተት ያ ድምጻችን ከነ-ወለዱ፣
የሕዝብ የሀገር ፍቱን ገመና ‘ብይን ፍርዱ’፤
እንዲባረክ የሰላም የትንሳዔው ውል ሰነዱ፤
ሰባው ሚሊዮን መርቆ፤አስታርቆ ሕዝብ-መሪዎች እንዲዋሃዱ።

የጐንቻው፣ yegonchaw@yahoo.co.uk

*ለዘመናት ከተፈጥሮ ሃብቱና ከመሪዎቹ ብቃት ለመቋደስና ለመጠቀም ያልታደለው ሁሉን ቻይ የኢትዩጵያ ሕዝብ ጠንክሮ በአምላክ ፈቃድና በራሱም ጥረት ከዚህ በኋላ በሕይዎቱና በኑሮው የሚወሰን እራሱ እንጅ የሚወሰንበት እንዳይሆን የመቻቻልና የአንድነት ልቦና ፈጥሮ ብሔራዊ እርቀ-ሰላም እንድያወርድ የመልካም ምኞት መግላጫና ማስተዋሻ ጭምር ትሁን።*